# ጽልመት

በሲሳይ ጌቴ

የሁቱ የዘር ግንድ የሆኑት የሩዋንዳው ፕሬዚዳንት ጁቬናል ሀብያሪማና ተሳፍረውበት የነበረው አውሮፕላን በተተኮሰ መሳሪያ ከተመታ በኋላ ህይወታቸው ማለፉ ይታወሳል። እ.ኤ.አ በ1993 የሁቱ እና የቱትሲ ጎሳ አባላት በጋራ የጥምር መንግስት ለማቋቋም የተጀመረው ጥረት ወደ ጎን ተገፋ። አክራሪ የሁቱ ጎሳ አባላት ቀደም ሲል በሁለቱ የጎሳ አባላት መካከል ተደርጎ የነበረውን የተኩስ አቁም ስምምነት በመጣስ ግጭቱ ተጀመረ። የሁቱ ጎሳ አባላት "እነርሱ በረሮዎች" እያሉ በሚጠሯቸው የቱትሲ የጎሳ አባላት ላይ እልቂት በመፈጸም "የመጨረሻውን ጦርነት" ወደ ተግባር አሸጋገሩት።

አካዙ (የሁቱ ጎሳ አባላት የፖለቲካ አመራሮች እና ልሂቃን) እየተባሉ የሚጠሩት የጅምላ ዘር ፍጅቱ ከመጀመሩ ቢያንስ ከአንድ ዓመት በፊት የቱትሲ ጎሳ አባላት የሆኑትን ሩዋንዳውያን ዜጎችን ለመፍጀት የታሰበበት ዕቅድ ነደፉ። የራሳቸውን ሬዲዮ ጣቢያ (ኮሊንስ) አቋቋሙ። እ.ኤ.አ በሚያዝያ 1994 ዓ.ም የዘር ማጥፋት ፍጅቱ በተጀመረበት ወቅት እነዚህ የሁቱ የፖለቲካ አመራሮች ሬዲዮ ጣቢያቸውን ነፍሰ ገዳዮችን ለማደፋፈር እና ለማበረታታት ይጠቀሙበት ጀመር።

ግድያ እንዲፈጸምባቸው ያዘጋጇቸውን የቱትሲ ጎሳ አባላት ስም ዝርዝር የሚያነቡበት እና እነዚያን ዘግናኝ የዘር ፍጅት ወንጀሎች እንዲፈጽሙ ለሚታዘዙ ገዳይ ሚሊሻዎች (ኢንተርሀሞይ እና ኢምፑዛሙጋምቢ) የትዕዛዝ መልዕክቶች የሚተላለፉበት ነበር።

ሁቱዎቹ በተደጋጋሚ በሬዲዮ ጣቢያው እንዲህ የሚል መልዕክት ያስተላልፉበት ነበር። "በእውነት ሁሉም የቱትሲ ጎሳ አባላት ከምድረ ገጽ መጥፋት አለባቸው፣ ቱትሲዎች ከዚህች አገር መጥፋት አለባቸው፣ ቱትሲዎችን እያነጣጠረ ለሚመታው መሳሪያ ምስጋና ይግባውና ቱትሲዎች ቀስ በቀስ በመጥፋት ላይ መገኘታቸው ብቻ አይደለም ዋናው ጉዳይ ሆኖም ግን እንደ አይጥ እየታደኑ መገደላቸው ጭምር እንጅ።"

እ.ኤ.አ በ1994 ከሩዋንዳ ከተማ ኪጋሊ በ30 ማይል ርቀት ላይ ከምትገኘው እና በሩዋንዳ ታላቅ ከተማ ከሆነችው ኒያማታ በምትባለው ከተማ የሚኖሩ 120 ሺህ የሩዋንዳ ዜጎቸ ነበሩ። ከአንድ

ወር እስከ አንድ ወር ከግማሽ ጊዜ ውስጥ በዚህች ከተማ ውስጥ 50 ሺህ ሰዎች ብቻ ቀሩ። ከስድስት ቱትሲዎች መካከል አምስቱ ይገደሉ ነበር። በሩዋንዳ በተካሄደው የዘር ማጥፋት ዘመቻ በመቶ ቀናት ውስጥ ከስምንት መቶ ሺህ እስከ አንድ ሚሊዮን የሚደርሱ ሰዎች አልቀዋል። እስከ 250 ሺህ የሚደርሱ ሴቶች ተደፍረዋል። የሀገሪቱን ህዝብ ለአሰቃቂ ሁኔታ ውስጥ እንዲያልፉ ተደርጓል። በርካታ  መሠረተ ልማቷም ወድሞባታል።
ይህ ሁሉ ሲፈጸም የአፍሪካ ህብረት እና የዓለም አቀፉ ማህበረሰብ፤ ዩናይትድ ስቴትስን እና የተባበሩት መንግስታትን ጨምሮ ከቁጥጥር ውጭ ወጥቶ ለነበረው የዘር ማጽዳት እልቂት እና ፍጅት ጆሮ ዳባ ልበስ የሚል ምላሽ ነበር የሰጡት።
ይህ ሁሉ አሰቃቂ ድርጊት የተፈፀመባት ሩዋንዳ ብሔራዊ መግበባት በመድረስ ከገባችበት ጽልመት መውጣት ችላለች። ትናንት የተደረጉ አጸያፊ ድርጊቶች ዛሬ ላይ ቦታ የላቸውም። ቂም፣ በቀል፣ ጥላቻ እና መገፋፋት ፈፅሞ አይታሰብም። ሩዋንዳዊያን ከገጠማቸው ስብራት መውጣት የቻሉበት ዋነኛው ምክንያታቸው ምክክር እና እርቀ ሰላም ማምጣት በመቻላቸው ነው ። ከዚህ በተጨማሪም ጥፋት በደረሰበት ወቅት ተሳታፊ የነበሩ አካላት ተጠያቂ በማድረግ የእርምት እርምጃ መውሰድ ተችሏል።
በአሁኑ ወቅት በአማራ ክልል የሰላም አየር ቀርቶ የጦርነት ንፋስ ነፍሶ ህብረተሰቡን ጽልመት ውስጥ ከትቶት ቆይቷል። የተፈጠረው ግጭትም የእርስ በርስ ከመሆኑ ባለፈ የኢኮኖሚ፣ ፖለቲካዊ፣ ማህበራዊ እና በሌሎች መስተጋብሮች ላይ ከፍተኛ ጉዳት እንዲደርስ አድርጎታል። አሁን ላይ በክልሉ ውስጥ ከፍተኛ የሆነ ሰብዓዊና ኢኮኖሚያዊ ጉዳት እየተስተናገደ ነው። በመሆኑም ሩዋንዳን እንደጥሩ ምሳሌነት በመውሰድ በመንግስትና በታጠቁ ሃይሎች መካከል ያላሰለሰ ጥረት ማድረግ፣ ችግሮችን በውይይትና በንግግር በመፍታት ሊደርስ የሚችለውን ጉዳት ከወዲሁ መቀነስና ማስቀም ይገባል።
የሩዋንዳውን የዘር ፍጅት ካባባሱት ውስጥ አንዱ ያቋቋሙት የሬዲዮ ጣቢያ ትልቅን ድርሻ ይወስዳል። የእኛም ሃገር የሚዲያ አጠቃቀም ውስንነት ስላለ በተለይም በማህበራዊ ሚዲያው የሚለቀቁ የጥላቻ ንግግር እና ሀሰተኛ መረጃዎችን በደንብ መመርመርና መረዳት ይገባል።

ግጭት ቀስቃሽ እና አባባሽ ሚዲያዎችን ባለመጠቀም እንዲሁም በመከላከልና በመቃወም ክልሉ የገጠመውን ቀውስ መቀልበስ ይቻላል፡፡

ሁሉም የህብረተሰብ ክፍል ልዩነቶችን ሊያሰፉ የሚችሉ የጥላቻ ቃላትን ወደጎን በመተው ክልሉ የገጠመውን ዘርፈ ብዙ ችግር በጋራ በመቆም በአንድነት መንፈስ መታደግ ይዋል ይደር የማይባል ጉዳይ መሆኑን ተረድተን በተባበረ ክንድ ክልሉን ከፍ ወዳለ የኢኮኖሚ ማማ መስቀል አስፈላጊ መሆኑን ተገንዝበን ከጥላቻ ይልቅ ሰላምን ለማስረፅ ራስን ማሳመን እና ማዘጋጀት ተገቢ ነው፡፡